

# ቀጭኗ መንገድ!





ግራውን ክንፍ ይዞ አንዱ ሲሞግት
ሌላም ቀኙን ይዞ ከዚያ ሲፎትት
እኔ እበልጥ! እኔ እበልጥ ሲሉ ሲጎትቱ
ገነጣጥለው ክንፏን ገደሏት ወፊቱ!

አስቀድሞ በፊት ግራ ክንፉ አየለ
የቀኙም ቀጥሎ በርትቶ ታገለ
የዝንጀሮ መንገድ ከገደል ያደርሳል
መቸውም የእልኽ ቤት አይረጋም፣ ይፈርሳል!

መሃል ረግጦ መሄድ እያለ ቀላሉ
መሃል-ሰፋሪ ነው፣ ፈሪ እንዳይባሉ
ግራ/ቀኝ መረጡ ገደላ-ገደሉ።
ምን ነበር ቢጓዙ መሃል-ለመሃሉ?

አላዋጣቸው ሲል ውሎ-አድሮ ገብቷቸው
አሁን ምን ያደርጋል፣ ምንስ ይዋጣቸው?
ግራ ክንፍ በቁጭት እራሱን ገደለ
ቀኙም በገበያ ሰርቆ ተሰቀለ





ግራ/ቀኝ እያሉ ሰው ከማሳሳት
በደጀ-ሰላሙ በርትቶ መግፋት
በጠባቢቱ በር ወደ ውስጥ መግባት
አይሻልም ወይ ከዚህ ከጥፋት?

ግራ/ቀኝ እያሉ ነገር ከሚያንዛዙ
ማታለሉን ትተው ቅንነቱን ቢይዙ
መካከሉን መንገድ በሰላም ቢጓዙ
ይሻላቸው ነበረ እጅጉን በብዙ!

ገ/ኢ. ጎርፉ።